የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ — ሰኔ ፭ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. 27
ADDIS ABABA - 12th June, 2001

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፴፱/፲፱፻፺፫ ዓ.ም
የፀረ–ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ (ማሻሻያ) አዋጅ ........................ ገጽ ፩ሺ፭፻፲፮

## CONTENTS

Proclamation No. 239/2001
Anti-Corruption Special Procedure and Rules of Evidence (Amendment) Proclamation .... Page 1516

## አዋጅ ቁጥር ፪፻፴፱/፲፱፻፺፫

## የፀረ–ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የፀረ–ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅን ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፀረ–ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፪፻፴፱/፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ማሻሻያ

በፀረ–ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር ፪፻፴፮/፲፱፻፺፫ በክፍል ሰባት ከአንቀጽ ፶፩ በፊት የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፶፩ ተጨምሮ፣ የቀድሞው አንቀጽ ፶፩፣ ፶፪ ፣ እና ፶፫ እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ ፶፪፣ ፶፫ እና ፶፬ ሆነዋል።

## PROCLAMATION NO. 239/2001

## A PROCLAMATION TO AMEND THE ANTI–CORRUPTION SPECIAL PROCEDURE AND RULES OF EVIDENCE PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Anti-Corruption Special Procedure and Rules of Evidence Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Fedeal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Anti-Corruption Special Procedure and Rules of Evidence (Amendment) Proclamation No. 239/2001".

2. *Amendment*

The following new Article 51 is included in Section Seven of the Anti-Corruption Special Procedure and Rules of Evidence Proclamtion No. 236/2001, and the previous Articles 51,52 and 53 are renumbered as Articles 52, 53 and 54 respectively.

"፶፩. ስለምርመራና ስለዋስትና

፩. የሙስና ወንጀልን የሚመለከት የመያዝ ፣ የብርበራ ፣ የቀነ ቀጠሮ ፣ በማረፊያ ቤት የማቆየት፣ የዕገዳ እና ሌላ ከምርመራ ጋር የተያያዘ ተመሣሣይ ጉዳዩን የሚመለከቱ ማመ ልከቻዎች ወይም ጥያቄዎች የሚታዩት የሙስና ወንጀል ጉዳይን ለማየት ሥልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት ይሆናል ።

፪. በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው የዋስትና መብት አይኖረውም።"

፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፭ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፭ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

"51. *Investigation and Bail*

1) Any application for arrest, search, remand, restraining or any other similar application or issue related to investigation of corruption offences shall be heard by the court which has a jurisdiction to hear cases of corruption offences.

2) A person who is arrested on suspicion of having committed a corruption offence shall not be released on bail."

3. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 12th day of June, 2001.

Done at Addis Ababa, this 12th day of June, 2001.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE